

## 33-2

# በራስ ፍቅር ከመያዝ እንሸሽ

### ሐ) ነብዩ ዮናስ

እግዚአብሔር የዮናስን ጠንካራ ልብና እምቢተኛነት ስለተረዳ የታዘዘውን እንዲሠራ ያደረገው ለ3 ቀናት ያህል እርሱነቱን ገድሎ በአሣነባሪ ሆድ ውስጥ ቀብሮ በመጨረሻ ትንሳኤን የሰጠው ነነዌ ከተማ ውስጥ ነው። ይህን የሚያደርገው በዮናስ ላይ ብቻ አይደለም። በእኛም ሕይወት ውስጥ ያደርጋል። አድርጉ የሚለንን ነገር ለማድረግ እንድንችል የራሳችንን ክብር ከእርሱ ክብር ጋር እንዳንቀላቅል በአንዳንድ አስቸጋሪ የሕይወት ፈተና ውስጥ እንድናልፍ አድርጎ እኛነታችንን ፈጽሞ እንድንገድል የሚያደርግበት ጊዜ አለ።

ዮናስ ከፍተኛ የአገልግሎት በር የተከፈተለት ሰው ነበር። የመጀመሪያው የወንጌል መልዕክተኛ (ሚሲዮናዊ) ሆኖ በዘመኑ በክብርና በታላቅነት እንዲሁም ገናና ወደ ነበረው ወደ ነነዌ ከተማ የንስሃን ቃል እንዲሰብክ የተላከ የእግዚአብሔር አምባሳደር ነበር። በአገልግሎቱም ከፍተኛ ውጤት ከነበራቸው ሰዎች ሁሉ ብልጫ ነበረው። በመልዕክቱም ተነክተው መላው የነነዌ ሕዝብ ማቅ ለብሰው በንስሃ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ ያደረገ ሰው ነበር። ይሁን እንጂ፥ ዓይኑን በራሱ ላይ ብቻ ያሳረፈ በራሱ ዝና፣ ስምና ክብር የተያዘ እንዲሁም ከራሱ ፍቅር ያልተላቀቀ ሰው ነበር። የነነዌ ሕዝብ ከኃጢአታቸው ንስሃ ገብተው ሊደርስባቸው ከነበረው መአትና መቅሰፍት በመዳናቸው ደስ ሊለው ሲገባ፥ የተናገረው ትንቢት ባለመፈጸሙ ሰዎች "ሀሰተኛ ነብይ ነው" ብለው ይተቹኛል፣ ይንቁኛል በማለት ቅሬታውን አሰማ። ዝናውና ስሙ ከሚጠፉ ይልቅ ቢሞት እንደሚሻለው በማሰብ መሬት ላይ ተደፍቶ "እግዚአብሔር ሆይ ግደለኝ" ሲል ጸለየ። ዮናስ የራሱን ክብር፣ ዝናና ስም ለእግዚአብሔር ብቻ ሊውል ከሚገባው አገልግሎት ጋር ሊቀላቅል ሲሞክር ይታያል። እግዚአብሔር የሚጠላው ነገር ቢኖር ትዕቢተኛውንና የእርሱን ክብር የሚሻማውን ነው።

### ከፍ ለማለት ዝቅ ማለትን ይጠይቃል

ዳዊት ብዙ ጊዜ ወድቋል፤ እጅግ አስከፊ ኃጢአቶችን ፈጽሞአል። በዓይን አዕምሮትና በፍትወት ምክንያት የሰው ሚስት ነጥቋል፤ ነፍስ ገድሏል። ይሁን እንጂ በድካሙ ተጸጽቶ መሬት ላይ ተንከባሎ እውነተኛ ንስሃ ገባ እንጂ እራሱን ፍጹም አድርጎ አላቀረበም። "አምላክ ሆይ! ስለ ዘላለማዊ ፍቅርህ ይቅር በለኝ፤ ስለ ታላቁ ምህረትህም ኃጢአቴ ደምስስልኝ። በደሌን ሁሉ አጥበህ አስወግድልኝ፤ ከኃጢአቴም አንጻኝ። እኔ ስህተቴን አውቄአለሁ፤ የኃጢአቴንም ብዛት ዘወትር እገነዘባለሁ። እኔ ያመጽሁት በአንተ ላይ ነው፤ የበደልሁትም አንተን ብቻ ነው። አንተ የምትጠላውን ነገር አደረግሁ፤ ስለዚህ በእኔ ላይ መፍረድህና እኔንም መቅጣትህ ትክክል ነው። ኃጢአተኛ ሆኜ እንደ ተወለድሁ ታውቃለህ፤ ከተጸነስሁበት ጊዜም ጀምሮ ኃጢአተኛ ነኝ" (መዝሙር 51፥1-5) አለ። እራሱን ዝቅ የሚያደርግ ሰው ስለ ነበር እግዚአብሔር "እንደ ልቤ የሆነውን ዳዊትን አገኘሁ" አለ።

ጴጥሮስ ችኩልና ሁልጊዜ እራሱን ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ለማስቀደም ልዩ መስሎ ለመ ታየት የሚሞክር ሰው ነበር። አንድ ጊዜ ክርስቶስ ተነበርክኮ የደቀ መዛሙርቱን እግር በሚያጥ ብበት ጊዜ የተቀሩት ደቀመዛሙርት እግራቸውን ኢየሱስ ሲያጥባቸው ዝም ሲሉ፥ እርሱ ግን "ፈጽሞ አንተ አታጥበኝም" ሲል እምቢ አለ። ከላይ ለሚመለከት ሰው የጴጥሮስ አባባል ጥሩ ይመስላል።ወደ ውስጥ ዘልቆ የሰውን ሕይወት መመልከት በሚችለው አምላክ ሲታይ ግን ይህን ያህል የጴጥሮስ እምቢ ማለት አስደሳች አልነበረም። ኢየሱስ እምቢ ያለበትን የተደበቀ ውስጣዊ ሀሳብ በደንብ አድርጎ ስለሚያውቅ ኢየሱስ "ካላጠብኩህ በመንግሥቴ ስፍራ የለህም" ያለው። በእርግጥም "ትልቅ ነኝ ከሌሎች የተሻልኩ ነኝ" የሚለውን የትዕቢት መንፈስ ከጴጥሮስ ሕይወት ታጥቦ መውጣት ነበረበት። አለበለዚያ እግዚአብሔር በሕይወቱ ሊያደርግ የወሰነው ዓላማ ግቡን አይመታም።

አንድ ወጣት ሰባኪ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ተንበርክኮ እንዴት እንዳጠበ ይሰብክ ነበር። በስብከቱ መካከል "ወገኖቼ ለመሆኑ ልብ ብላችኋል? ሁላችንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛውን ደረጃ ለመያዝ ምን ያህል እንደምንታገል ፎጣውንና የማጠቢያውን ሳህን ይዘን "እኔ ካላጠብኩ" በማለት የምንታገል ግን በመካከላችን ማንም እንደሌለ ልብ ብላችኋል?" ሲል አስተያየቱን ሰጠ። እርግጥ ነው በክርስቲያኖች መካከል የመጨረሻ ከሁሉም ዝቅተኛና አነስተኛ ለመሆን እራሳችውን የሚሰጡ በጣም ጥቂቶች ናቸው። ይህን እንዲህ ሊሆን የቻለው ዝቅ በማለት ውስጥ ያለውን አሸናፊነት ስለ አልተገነዘብን ብቻ ነው። ዲ ኤል ሙዲ "እራሳችንን እስከ መጨረሻ ወደ ታች ዝቅ ብናደርግ እግዚአብሔር ለክብሩ በተጠቀመብን ነበር" አለ።

ጴጥሮስ ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ለየት ብሎ የመታየት እራሱን የማተለቅ ችግር እንዳለበት የታየው ክርስቶስን "ሌሎች ደቀ መዛሙርት ቢክዱህም እኔ ግን እሞትልሃለሁ" ሲለው ነው። ይሁን እንጂ በአንድ ምሽት ሦስት ጊዜ ጌታውን ሲክዳ የተሰማው የበደለኛነት ስሜት፣ ያፈሰሰው ዕንባ በስቅላቱ ወቅት የነበረው መራራ ጊዜ፣ ጴጥሮስ የራሱን ባዶነት እንዲረዳና እራሱን ወደታች ዝቅ አድርጎ በአምላኩ ጸጋ ውስጥ ብቻ መኖርን ተማረ። ዝቅ ማለትን ለማስተማር አንድ ጸሐፊ እንዲህ አለ። "እራስህን አትመነው፣ ዕቅድህ፣ ትጋትህ፣ እንዲሁም የምታገኛቸው ድሎች አያታሉህ። በእግዚአብሔር ፊት እራስህን ዝቅ አድርጎ የመመልከት ባህሪ ይኑርህ። ከዚህ ሁሉ በላይ አድናቂዎችህ የሚያጎርፉልህን የሙገሳ ቃል ጨርሶ አትስማ። ይህን ባታደርግና በምትሰ ማው የሙገሳ ቃል ብትሸነፍ፣ ያገኘኸው ድል እውነተኛ ሳይሆን በውጪ የሚታይ ብቻ ነውና አገልግሎትህን ብታቆም ይሻልሃል። ሰዎች ከፍተኛ ቦታ ቢሰጡህም በእግዚአብሔር ፊት የሚኖርህ ቦታ በጣም አነስተኛ ነው" አለ።

**"በራሱ ፍቅር" የተጠመደ ሰው ባህሪ**

1) **እራሱን እንደ ፍጹም ያያል**

"በራስ ላይ ያተኮረ" ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች፥ ምንም እንኳን ሁልጊዜ የሚሠሩት ሥራ ልክ እንዳልሆነ ቢያውቁም፥ ስህተታቸውን መቀበል ያቅታቸዋል። ሼክስፔር "እራሳቸውን ከሚያሞ ጋግሱ ሰዎች መካከል አንድም አዋቂ ሰው አይገኝበትም" ይላል። የእግዚአብሔር ቃልም ስለ እራሳቸው ከሚገባው በላይ ትልቅ ግምት ያላቸውን ማስጠንቀቂያ ይሰጣል። "ራሳችሁን ብልህና ጥበበኞች አድርጋችሁ ለምትቆጥሩ ውዮላችሁ" (ኢሳያስ 4፥21) ይላል። ይሁን እንጂ ማስጠንቀቂያው እነርሱን የሚመለከት አይመስላቸውም። በተግባርም ሆነ በንግግር ብዙ ጊዜ ሰዎችን መጉዳታቸውን ቢያውቁም እራሳቸውን በማስተካከል ፈንታ ቶሎ "እራሳቸውን ይቅር ብለው" እንደ ቀድሞአቸው ይቀጥላሉ።

**2) ከሌሎች ተሽሎ መታየት ይፈልጋል**

በራሱ ፍቅር የተያዘ ሰው፥ ከሌሎች ተሽሎ ለመታየት ብቻ ሲል ምንም ዓይነት ዋጋ ለመክፈል ወደ ኋላ አይልም። በዚህ ምክንያት አቅሙ ከሚፈቅድለት በላይ ለመኖር ሲታገል ይታያል። በገቢው መጠን በመኖር ፈንታ ተበድሮም ሆነ ተለቅቶ የውጪውን ሲያሰማምር ቤተሰቡን ግን ሲጎዳ ይገኛል። “ሀብታም መስሎ በችግር ከሚኖር ሰው ይልቅ ተራ ሰው መስሎ እየሠራ ኑሮውን የሚያሸንፍ ይሻላል” (ምሳሌ 12፥9) የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ለእርሱ ጊዜ ያለፈበት ምክር ሆኖ ይታየዋል። ክላርክ የተባለ ጸሀፊ “ከውሸት ሁሉ አሳፋሪውና አስነዋሪው፥ በምላሳችን የምንናገረው ውሸት ሳይሆን፥ የምንኖረው የውሸት ኑሮ ነው” አለ።

**3) “በሁሉም ነገር ልክ ነኝ” ይላል**

“ልክ አይደለህም! ተሳስተሃል!” ተብሎ እንዲነገረው አይፈልግም። መጽሐፍ ቅዱስ “ትዕብተኛን ሰው ብታርመው ስድብን ታተርፋለህ” (ምሳሌ 9፥7) ይላል። መሳሳቱንም ቢያውቅ “ተሳስቻለሁ፤ ይቅርታ!” ማለት ጨርሶ አይሆንለትም። አለማወቁን ተረድቶ ወደ ማወቅ የሚያደር ሰውን እርምጃ በመውሰድ ፈንታ አለማወቁን ከሰዎች ለመደበቅ ሲል አላዋቂ ሆኖ ይቀራል። ፐሉተርክ የተባለው ጸሀፊ “ሁሉን ማድረግ አለመቻል ነውር የለበትም፤ ማድረግ የማንችለው፣ እንደምንችል አድርገን ማስመሰል ግን አስነዋሪና አሳፋሪ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ችግርና አዘቅት ውስጥም ይከታል” አለ።

**4) ስለራሱ ብዙ ያወራል**

ቅዱስ አውጉስቲን አንድ ጊዜ “ከእምነት ውስጥ ትልቁ ነገር ምንድነው?” ተብሎ ተጠይቆ ሲመልስ “ከሃይማኖት ትልቁ ነገር አንደኛውም፣ ሁለተኛውም እንዲሁም ሦስተኛው ትህትና ነው፤ ከእርሱ የሚበልጥ ምንም ነገር የለም” አለ። በራሱ ፍቅር የተያዘ ሰው የሚያወራው ያደርገውን የሠራውንና ያገኘውን ድል ብቻ ነው። ሰሚው የእርሱን ጀብዱ ብቻ መስማት ይሰለቸዋል ብሎ አይገምትም። ማንነቱን ለሌሎች የመግለጽ ዕድል እስከ አገኘ ድረስ ሰሚዎች ቢሰለቻቸውም ግድ የለውም። አንድ ጊዜ ቻይና ውስጥ ሁለት ቻይናውያን ሴቶች መጀመሪያ ለቻይናውያን ወንጌልን ለመስበክ የመጣውን የወንጌል መልዕክተኛ (ሚሲዮናዊ) ሚስተር ቴይለርን እያደነቁ ያወሩ ነበር።  አንደኛዋ “ለመሆኑ ሚስተር ቴይለር ኩራት ተስምቶት ያውቃል?” ስትል ጠየቀች። ለጥያቄያቸው መልስ ለመፈለግ ሚስቱን ሄደው “ ለመሆኑ ባልሽ ሚስተር ቴይለር ኩራት ተስምቶት ያውቃል?” ሲሉ ጠይቋት። “እኔ እንጃ! አላውቅም” ስትል መለሰችላቸው። ነገሩ አስደንቃትና እርሷም በተራዋ ኩራት ተስምቶት ያውቅ እንደ ሆነ ጠይቀቻቸው። ሚስትር ቴለርም ሲመልስ፥ “ኩራት! ስለምኑ ነው? ምን አድርግሁና!” ሲል መለሰ። ሚስቱም ስትመልስ “በሕይወትህ ስለ አድረግኸው ነገር” አለቻቸው። እርሱም “ምንም ማድረጌን አላውቅም” ሲል መለሰላት። እውነቱን ነው! እግዚአብሔር በሕይወቱ ሠራ እንጂ በራሱ ኃይልና ጉልበት ምንም የሠራው ነገር የለም። በራሱ ፍቅር የታሠረ ሰው እግዚአብሔር ያደርገውን ነገር በማውራት ፈንታ እርሱ ያደርገውን መናገር ይቀለዋል። የመናገር ዕድል ባገኘ ቁጥር የሚናገረው ምን ይሃል በሽተኞች እርሱ ጸልዮላቸው እንደተፈወሱ ምን ያህል ሰዎች እርሱ ሰብኮላቸው እንደ ዳኑ በምስክርነት መልክ በመግጽ ያን ያህል መንፈሳዊ እንደ ሆነ ለማሳየት ይሞክራል። ዲ ኤል ሙዲ “አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ብዙ ርቆ እንደሄደ ማወቅ የሚቻለው ስለ ራሱና እንዲሁም ስለ እራሱ ጥሩነት ብዙ የተናገር እንደሆነ ነው” አለ።

**5) በቀላሉ ይጎዳል**

በራሱ ፍቅር የተያዘ ሰው ስሜቱ በቀላሉ ይጎዳል። ሁልጊዜ ማደግ፣ መበለጥ እንዲሁም ከሌሎች የተሻለ ሆኖ መታየት ስለሚፈልግ የሚበልጠውን ሰው ሲያይ ስሜቱ ይደፈረሳል።

መልካም ንግግር እንኳን "አታውቅም" የተባለ ስለሚመስለው በቀላሉ ይቆጣል። ሰለሞን "የሞኝ ቁጣ ወዲያው ይታወቃል፤ ብልህ ሰው ግን በእርሱ ላይ የተሰነዘረውን ስድብ ችላ ይላል" አለ (ምሳሌ 12፥16)። እንዲሁም ቦቪ የተባለው ደግሞ "በቀላሉ የሚጎዳ ሰው በራሱ ፍቅር የታሠረ ነው፤ አለአግባብ በቀላሉ ይበረግጋል፤ ከዚህ ለመዳን ቢፈልግ ዓይኑን ከራሱ ላይ አንስቶ ሌላ ነገ ይመልከት" ይላል።

6) **ከሰው ጋር መኖር አይሆንለትም**

"እኔ ያልኩት ካልሆነ፣ የእኔ ፍላጎት ብቻ ካልተሟላ" ይላል። የራሱን እንጂ የሌላውን ሰው ፍላ ጎት ዓይኑ ተከፍቶለት ማየት አይችልም። በዚህ ምክንያት ብዙ ጊዜ ከሰው ጋር ይጋጫል። በጋ ብቻ ውስጥ እራስ ወዳድነት ካለ በሰላም ከኑሮ ጓደኛ ጋር መኖር አይቻልም። መጽሐፍ ቅዱስ "የራስ ወዳድ የሆኑ ሰዎች ከሌሎች ጋር ተስማምተው መኖር አይሆንላቸውም፤ ሌሎች ሰዎች ትክክል መሆኑን አውቀው የሚያምኑበትን ነገር እነርሱ ይቃወማሉ" ይላል (ምሳሌ 18፥1-2)።

**ራስ ወዳድነት የሚያመጣው ጉዳት**

-እርሱን የሚወድ ሰው እግዚአብሔርን አለማክበሩ ብቻ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ዙፋንና ስልጣን "እኔ ካልያዝኩ" ሲል ይሻማል።

-ራስ ወዳድነት የኃጢአት ሁሉ መግቢያ በር ነው። የራሱን ልብ በራሱ ኃይል ለመጠበቅ የሚሞ ክር ሰው እራሱን ለኃጢአት ፈተና አጋልጦ ይሰጣል። ራስ ወዳድ መሆን በሰይጣን ግዛት ውስጥ መኖር ማለት ነው።

-ራስ ወዳድነት ፍቅርንና አንድነትን ያጠፋል። ራስ ወዳድነት የጠብ፣ የጥላቻ፣ የጥርጣሬ፣ የምቀኝነትና የቅናት ሁሉ ዋና ምንጭ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመከፋፈልና የመገነ ጣጠል ትልቁ ምክንያት በራስ ወደድነት ምክንያት የሚፈጠረው ግጭት ነው። ራስ ወዳድነት ጎልቶ በሚታይበት ሥፍራ አንድነት ሰላምና ስምምነት አይኖርም።

..........................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**